# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 96 መጋቢት 9 2002 ዓ.ም


ምርጫን እንደመሰለያ መሳሪያ የሚጠቀመው ወያኔ በድህረ ምርጫ 97 በህዝባችን ላይ የፈጸመው አይነት ፋሽስታዊ ጭፍጨፋ እንዳይደገም ከተፈለገ፣ ነጻ እና ገለልተኛ የሆነ የምርጫ አስፈጻሚ አካላት፤ ለሁሉም እኩል የሚያገለግል የሚዲያ አገልግሎት፤ ታማኝነታቸው ለህገመንግሥቱ ብቻ የሆነና ከፖለቲካ ወገናዊነት የጸዱ የፖሊስ፤ የመከላኪያና የደህንነት ተቋማት መመስረት ይኖርበታል።

ለወያኔ እድሜ መራዘሚያ ህጋዊና ሞራላዊ መሰረት እንዲያስገኝ ታስቦ በሚካሄድ ምርጫ መሳተፍ ለህዝባችን የሚያስገኘው ፋይዳ አይኖርም!!!

## ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ የሚፈጽመውን ሰቆቃ የሚያጋልጥ ስብሰባ በታላቋ ብርታኒያ ፓርላማ ውስጥ ተካሄደ

ባለፈው ሰኞ የመጋቢት6 ቀን 2002 ዓም 'የሰብአዊ መብት ጥሰትና የዘር ማጥፋት ወንጀል በኢትዮጵያ' በሚል ርእስ በታላቋ ብሪታንያ ፓርላማ ውስጥ አንድ ታላቅ ስብሰባ መካሄዱንና ስብሰባውም የተዘጋጀው የሁሉም ፓርቲዎች የፓርላማ ቡድን አባላት ያሉት የሶስተኛው ዓለም ትብብር በተሰኘ ድርጅት አሰባሳቢነት መሆኑ ታውቋአል።። በዚህ ስብሰባ ላይ በእንግሊዝ ነዋሪ የሆኑ በርካታ ኢትዮጵያዊያን ተሳትፈው እንደነበር ተያይዞ ተዘግቦአል።

የሁሉም ፓርቲዎች ቡድን የ3ኛው ዓለም ትብብር ሊቀመንበር በሆኑት ካውንስለር ሙሽታክ ላሺር የስብሰባ መሪነት በዚሁ በለንደን በተካሄደው ታላቅ ህዝባዊ ስብሰባ፣ በምርጫ 97 የአውሮፓን የምርጫ ታዛቢ ቡድን የመሩት የአውሮፓ ህብረት የፓርላማ አባል የተከበሩ ወይዘሮ አና ጎሜዝ እና የኣዲሲቷ ኢትዮጵያ የወዳጂነት ንቅናቄ ዳይሬክተርና ኢትዮጵያዊው የሰባዊ መብት ተሟጋች አባንግ ሜቶ በተናጋሪ እንግድነት የተገኙ ሲሆን የእንግሊዝ ፓርላማ አባላት ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች፤ ጋዜጠኞች፤ የኢጋዴን ሶማሊያ ተወላጆች፤ የኢትዮጵያ ወዳጆች የሆኑ የተለያዩ ሃገራት ዜጎችና በርካታ ኢትዮጵያዊያን ተገኝተዋል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ኢትዮጵያ ወደ ወታደራዊ አገዛዝ እየገባች ነው ሲል ታዋቂው ዘ ኢንዲፐንደንት ጋዜጣ ዘገበ

ኢንዲፐንደት ጠለፋ፣ አስገድዶ መድፈር፣ ጋብቻ፤ የኢትዮጵያ ሴቶች ነጻ ይወጡ ይሆን? በሚል ርእስ ባሰፈረው ጽሁፍ አምባገነኑ መለስ ዜናዊ አገሪቱን ወደ ወታደራዊ አገዛዝ እየለወጣት በመምጣቱ በሴቶች ላይ የሚደርሰው ጭቆና ተባብሶ እንዲቀጥል ምክንያት ሆኗል ብሎአል።

ኢንዲፐንደንት ለንባብ ባበቃው በዚህ ዘገባው "ማንኛውንም ታክሲ ሾፌር ወይም መንገደኛ ሰው አግኝታችሁ ስለመለስ ዜናዊ ምን ታስባለህ ብትሉት እየተንቀጠቀጠ እና እየፈራ ጥሎአችሁ ይጠፋል" ሲል በአገሪቱ የሰፈነውን የፍርሀት ድባብ ከባድነት አጋልጧል። የመገናኛ ብዙሀኑ በአለቆቻቸው ተጽፎ የተሰጣቸውን ፕሮፓጋንዳ ብቻ እንደሚያስተላልፉ የገለጸው ኢንዲፐንደንት፣ "የቀድሞው የማርኪሲስት የጫካ ተዋጊ የነበረው መለስ ዜናዊ አንድም ቀን እውነተኛ ዴሞክራት ሆኖ አያውቅም ብቻ ሳይሆን ከ97 ምርጫ ጀምሮ በአገሪቱ ውስጥ የነበረውን ነጻነት አዳፍኖታል" ሲል አትቷል። አገዛዙን የሚተቹት ቡድኖች ከአገር ተሰደዋል ወይም ሰቆቃ ተፈጽሞባቸው አርፈው እንዲቀመጡ ተደርገዋል የሚለው የጋዜጣው ዘገባ፣ ለአንድ አምባገነን አገዛዝ የተደራጁ ሀይሎች ምን ጊዜም በእጅጉ ያስፈሩታል ሲል የመለስ ዜናዊን አገዛዝ ከፋኛ ተችቷል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## አምባገነኑ መለስ ዜናዊ ፎቶ ግራፉን በየከተሞች ማሰቀል ጀመረ፤ ስሙን የሚያሞካሹ ዘፈኖችንም ማሰራ ጨት ተጀምሮአል

ሪፖርተራችን ከአዲስ አበባ በላከው መረጃ እንዳመለከተው በተለያዩ የአዲስ አበባ ከተሞች እና በሁሉም የመንግስት መስሪያቤቶች የመለስ ዜናዊ ፎቶ ግራፍ እንዲሰቀል እየተደረገ ነው። የተለያዩ የመንግስት መስሪያቤቶችን በመጎብኘት ለማረጋገጥ እንደቻለው፣ የመለስ ዜናዊ ፎቶግራፍ በተለያዩ የሲቪል ሰርቪስ መስሪአቤቶች ውስጥ ግድግዳ ላይ ተለጥፎ ይገኛል። ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ ደግሞ በአዲስ አበባ የተለያዩ ማእዘናት ፎቶግራፉ በመንጠልጠል ላይ ነው። ድርጊቱ በመንግስቱ ሀይለማርያም ዘመን የነበሩትን የመጨረሻ አመታቶች ያስታውሳናል ያለው ሪፖርተራችን፣ መለስ አንበሳ የሚል ሙዚቃ በየደባባዩ እንዲሳማ ማድረጉ ሰውየው ወደየት እያመራ እንደሚገኝ ያመለክታል ብሎአል። በግንቦት97 ምርጫ ወቀት በጊዜው የአዲስ አበባ ከንቲባ የነበሩት አቶ አርከበ እቁባይ የኤድስ ምርመራ ሲያደርጉ የተነሱትን ፎቶ ግራፍ ቼርችል ጎዳና ላይ በማሰቀላቸው የተበሳጨው መለስ ዜናዊ ፎቶግራፉ በአንድ ምሽት እንዲወርድ ማስደረጉና በአርከበ ላይም እርምጃ መውሰዱ ይታወሳል። መለስ ዜናዊ አንበሳ የሚለው ዘፈን በትግራይ መስተዳደር ድህረ ገጽ ፊት ለፊት ተቀምጦ ለማየት ይቻላል።

በተያያዘ ዜናም ወያኔ በምርጫ 97 ማግስት ሲያደርገው እንደነበረው ሁሉ አሁንም የአዲስ አበባን ወጣቶች በስብሰባና በተለያዩ (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

ግዜ ግንቦት 7 ዜና

## የወያኔ የደህንነት ባለስልጣን ጌታቸው አሰፋ የስለላ ሰራተኞቹን ሰብስቦ ጥብቅ ት ዕዛዝ አስተላለፈ

የነፍሰ ገዳዩንና አምባገነኑን መለስ ዜናዊ ሥልጣን ዕድሜ ለማራዘም በወያኔ ታማኝ የስለላ ሰራተኞች የተማከለው የደህንነትና ኤሚግሬሽን ሃላፊ ጌታቸው አሰፋ ባለፈው ሳምንት መጨረሻ ላይ ስብሰባ ጠርቶ በአገዛዙ ላይ ማንኛውንም ዓይነት ተቃውሞ የሚያደራጁትን በጥብቅ እንዲከታተሉና አፋጣኝ የሆነ የአፈና እርምጃ እንዲወስዱ ጥብቅ ትዕዛዝ ማስተላለፉን ለደህንነት መሥሪያ ቤቱ ቅርበት ያላቸው ምንጮቻችን ከላኩልን መረጃ ለማወቅ ተችሎአል።

ከአገር ውስጥና ውጭ ለተጠሩት የደህንነት ሠራተኞች በተዘጋጀው በዚህ ስብሰባ ላይ በፊታችን ግንቦት ወር ይካሄዳል ተብሎ የሚታሰበውን የይስሙላ ምርጫ ተከትሎ አክራሪ በሚሉዋቸው የውስጥና የውጭ ተቃዋሚ ሃይሎች አቀነባባሪነት የአገዛዙን ህሊውና ሊፈታተን የሚችል ህዝባዊ አመጽ ሊቀሰቀስ እንደሚችል ያለው ስጋት ተገልጾ ይህ ከመሆኑ በፊት አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ እንዲቻል ከያንዳንዱ የደህንነት ሠራተኛ ከፍተኛ ወገናዊነት እንደሚጠበቅ ማሳሰቢያ ተሰጥቶአል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የወያኔ ፍርድ ቤት በእነ ጄኔራል ተፈራ ማሞ ላይ የቀረበውን የይግባኝ ጥያቄ ለማየት ቀጠሮ ሰጠ

በመለስ ዜናዊ ታማኝ ሰዎች የሚሽከረከረው የጠቅላይ ፍርድ ቤት ከአቃቤ ህግ የቀረበለትን ጥያቄ በመቀበል በእነ ጄኔራል ተፈራና ሌሎች ንጹሀን ዜጎች ላይ የሞት ፍርድ ለመወሰን ቀጠሮ መያዙን ያገኘነው መረጃ አመልክቷል። ከግንቦት7 ጋር በማበር መፈንቅለ መንግስት ሊያደርሱ ሲሉ ተያዙ የተባሉት እነኚህ ታጋይ ኢትዮጵያውያን፣ ቀደም ብሎ በይስሙላ ፍርድ ቤት የእድሜልክ እስራት የተወሰነባቸው መሆኑ የሚታወስ ሲሆን፣ ይህን ፍርድ በመቃወምም አቃቢ ህግ ይግባኝ መጠየቁን መዘገባችን ይታወሳል። ድሮውንም ከፍተኛው ፍርድ ቤት ፍትህ አለ ለማሰባል ሲል በእስረኞቹ ላይ የእድሜልክ እስራት ፍርድ ወስነ እንጅ፣ የህወሀት ባለስልጣናት የመጨረሻ ፍላጎት ሰዎቹ በሞት እንዲቀጡ ነው የሚሉት አንዳንድ ቤተሰቦች፣ አቃቢ ህግ ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት ሊያገኝ እንደሚችልም ተናግረዋል።

የአሜሪካ የስቴት ዲፓርትመንት ሰሞኑን ባወጣው ሪፖርት እነ ጄ/ል ተፈራ ማሞ በእስር ቤት ውስጥ ከፍተኛ የሆነ ስቃይ እንደተፈጸመባቸው መግለጹ ይታወሳል።

## የአሜሪካን ስቴት ዲፓርትሜንት በኢትዮጵያ ያለው የሰብአዊ መብት ረገጣ ተባብሶ መቀጠሉን ገለጸ

የአሜሪካን ስቴት ዲፓርትሜንት በአለም ዙሪያ ያለውን የሰብአዊ መብቶች አያያዝ በተመለከተ ሰሞኑን ይፋ ባደረገው ሪፖርት፣ በኢትዮጵያ ያለው የሰብአዊ መብቶች አያያዝ መሻሻል እንዳላሳየ ገልጿል። በአለፈው የፈረንጆች አመት በኢትዮጵያ ከታዩት ከፍተኛ የሆኑ የመብት ጥሰቶች መካከል ንጹሃን ዜጎችን መግደል፤ እስረኞችን ማሰቃየት፣ ድብደባዎችን መፈጸም፤ የተቃዋሚ ፓርቲ አባላትንና ደጋፊዎችን በአገዛዙ ታጣቂ ሃይሎች ማዋከብ፤ ደረጃቸው በማይታመን ሁኔታ በወረዱ እስር ቤቶች ዜጎችን በግፍ ማሰቃየት፤ ያለምንም በቂ ምክንያትና የፍርድ ቤት ትእዛዝ ግለሰቦችን ወደ እስር ቤት ማጎር፤ የፕሬስ ነጻነትን በእጂጉ ማፈን፣ የሴቶችና የህጻናት መብቶች መደፈር የሚሉት ይገኙበታል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## በባህርዳር እና በመቀሌ ከተሞች ወታደራዊ ሹም ሽር መደረጉ ተሰማ

ከየካቲት 23 እስከ የካቲት 28 ቀን፣ 2002 ዓም በሙሉአለም አዳራሽና በመቀሌ ከተማ በተደረገው ወታደራዊ ስብሰባዎች አገዛዙን ለማፍረስ ይንቀሳቀሳሉ የተባሉ ወታደራዊ መኮንኖች ማእረጋቸውን የተነጠቁ ሲሆኑ፣ ለአገዛዙ ታማኝ ናቸው የተባሉት የሰራዊቱ አባላት ደግሞ ከሙቶ አለቅነት ጀምሮ ያሉ የማእረግ እድገቶች ተሰጥቶአቸዋል።

በልዩ ጥበቃ የተከናወነው የመኮንኖች ግምገማና ሹም ሽር ከእነ ብርጋዴር ጄኔራል ተፈራ ማሞ ጋር ንክኪ አላቸው ተብለው የተጠረጠሩ እንዲሁም ከተቃዋሚዎች ጋር በመሆን አገዛዙን ይወጋሉ የተባሉ መኮንኖች ማእረጋቸውን እና ስራቸውን እንዲያጡ እንደተደረገ ያገኘነው መረጃ አመልክቶአል።

በአሁኑ ሹም ሽር ሲጠበቅ እንደነበረው አብዛኛውን ማእረግ የተቀበሉት ታማኝ የህወሀት ወታደሮች ሲሆኑ በአንጻሩ ደግሞ ማእረጋቸውንና ስራቸውን የተነጠቁት የአማራ ተወላጅ መኮንኖች መሆናቸው ታውቋል።

ከወታደራዊ ምንጮቻችን ያገኘው መረጃ እንደሚያሳየው፣ የወታደሩ ግምገማ ያነጣጠረው በሰሜኑ ያገራችን ክፍል እየተጠናከረ የመጣውን የተቃዋሚዎች እንቅስቃሴ ለመግታት ስለሚቻልበት ሁኔታና ስለምርጫው ሂደት ነበር።

(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ምርጫ 97 በ2002 ዓ.ም በትግራይ

ምርጫ 97 ኢትዮጵያዊያን ለዲሞክራሲ ያላቸውን ጥማት እና በጠመንጃ ኃይል ሥልጣን ላይ የወጣውን ወያኔን በምርጫ ካርድ ለማውረድ የነበራቸውን ጉጉት ያሳዩበት ነበር። በተጨማሪም ኢትዮጵያዊያን ውስጥም ብትሆን ነፃነት ካገኙ የመቶ ዓመታት ልምድ ካካበቱ አገሮች ሕዝቦች ባላነሰ ጨዋነት በተሞላበት ሥነ-ሥርዓት የሚበጃቸውን ለመምረጥ የማይቸገሩ መሆኑ እና ድምፃቸውን ለማስከበር መስዋዕትነት ለመክፈል የተዘጋጁ መኖራቸውን በግልጽ አሳይቶናል። ምርጫ 97 በኢትዮጵያ የፓለቲካ ታሪክ ውስጥ ሁነኛ ቦታ ይዞ እንደሚቆይ አንዳችም ጥርጥር የለም። ያን የመሰለ በቅን መንፈስ የተነሳሳን ሰላማዊ የለውጥ እንቅስቃሴ ፍጹም አረመኔያዊ በሆነ አፈና በመደፍጠጡ ከተገኙ ትምህርቶች አንዱ ወያኔን በምርጫ ካርድ ማስወገድ የማይቻል መሆኑን ነው።

ይሁን እንጂ የምርጫ 97 ግለት እና ከእርሱም የተገኘው ትምህርት በሁሉም የአገራችን ክልሎች እኩል አሊያም ተመሳሳይ ነበር ማለት አይቻልም። በተለይም የትግራይና የሶማሌ ክልሎች ምርጫ 97 እና እሱን ተከትለው በመጡ ኩነቶች አንፃር ከሌሎች የአገራችን ክፍሎች የተለየ መልክ ይዘዋል።

በ1997 እና 1998 አብዛኛው የሃገሪቱ ክፍል ምርጫው በፈጠረው የለውጥ ፍላጎትና እና በወያኔ አረመኔያዊ እርምጃዎች ሲናጥ ትግራይ ውስጥ ምርጫን በተመለከተ የረባ እንቅስቃሴ አልነበረም። ምርጫ 97 ለትግራይ ከተለመዱ የወያኔ ክብረ በዓሎች እንደ አንዱ ነበር ማለት ይቻላል። ትግራይ ካሏት 38 የፌደራል ፓርላማ መቀመጫዎች 17ቱ ማለት በ45 ከመቶ የምርጫ ወረዳዎች ወያኔ ያለምንም ተወዳዳሪ ብቻውን ሮጦ በማሸነፉ ሲጨፍር ነው የሰነበተው። በተቀሩት 21 የምርጫ ወረዳዎች ውስጥም አንዳችም ሁነኛ ተፎካካሪ አልነበረውም። የክልል ምክር ቤት ምርጫን በተመለከተ ሁኔታው ከዚህ በእጅጉ የባሰ ነበር። በዚህም ምክንያት ወያኔ የትግራይን የፌደራልም ሆነ የክልል ወንበሮችን ጠቅልሎ እንደያዘ ቀጠለ። ይህም ሆኖ ግን በትግራይ ውስጥ ሁኔታዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊቀየሩ እንደሚችሉ በርካታ አመላካቾች ነበሩ። በአዲስ አበባና ሌሎች ከተሞች ነዋሪ የሆኑ የትግራይ ተወላጆች ከሌላው ሕዝብ ጋር ተመሳሳይ በሆነ መንገድ ለውጥን በመደገፍ የሰጡት ድምፅ አንዱ ትልቁ ተስፋ ሰጭ አመላካች ነበር። ከምርጫ 97 በፊት የተጀመረ፤ በክልሉ ተወላጆች የተደራጀ ፀረ-ወያኔ የትጥቅ ትግል መኖሩ ሌላው አቢይ አመላካች ነበር፤ አሁንም ነው። ያም ሆኖ ግን ምርጫ 97 በተመለከተ ትግራይ ክልል ሌላ ቦታ ስለሚደረጉ የተሟሟቁ ውድድሮች ዜናዎችን ብቻ ነው የሰማችው ማለት ይቻላል።

ዘንድሮ ሁኔታው ተቀይሯል። በሌላው የአገራችን ክፍሎች በ97ዓ. ም. የነበረው ለምርጫ መነቃቃት ዘንድሮ ወደ ትግራይ ዘልቋል። በዘንድሮው ምርጫ ወያኔ ትግራይ ውስጥ ብርቱ ባላንጣዎች ገጥመውታል። ከ38ቱ መቀመጫዎች ከ30ዎቹ በላይ ብርቱ ውስጥ ገብተዋል።

ወያኔ ከምርጫ 97 የተማረው ምን እንደሆነ አሁን በትግራይ ውስጥ እያሳየን ነው። በምርጫ 97 ግድያ የተጀመረው በምርጫው ማግስት ነበር። ዘንድሮ ትግራይ ውስጥ ግድያን ከምርጫው ሁለት ወራት አስቀድሞ ጀመረ። አገዳደሉም የእጅ አዙር፣ አሰቃቂና ነውረኛ እንዲሆን አደረገ። ይህ ወያኔ ከምርጫ 97 የቀሰመው አንዱ ትምህርት መሆኑ ነው።

በምርጫ 97 ፍርድ ቤቶች የምርጫው ተውኔት አቢይ አካል የሆኑት ከምርጫው በኋላ አንድ ዓመት ያህል ዘግይተው ነው። ዘንድሮ በትግራይ ፍርድ ቤቶች ከድምፅ መስጠት በፊት የተወናው አቢይ አካል ሆነዋል። ለዚህም ማረጋገጫ አቶ አረጋዊ ገብረዮሃንስ በአሰቃቂ ሁኔታ በተገደሉ በሁለት ሣምታት ውስጥ ወያኔ ለጭዳነት ባቀረበው አንዱ አገልጋይ ላይ ፈጣን ብይን መስጠቱ ነው። የሰው ሕይወት ያለፈበት የፍርድ ሂደት በእንዲህ ዓይነት ፍጥነት ሲሰጥ በኢትዮጵያ ታሪክ የመጀመሪያ ነው። ከገዳዮች አንዱ የአቃቤ ህግ ምስክር ሆኖ መቅረቡም ችሎቱን በዓለም-ዓቀፍ ደረጃም ልዩ ያደርገዋል። ለነገሩ አቶ አረጋዊ ሕይወታቸው ባለፈ ጥቂት ሰዓታት ጊዜ ውስጥ "የተገደሉት በቡና ቤት በተነሳ ተራ ጠብ ምክንያት ነው" በማለት የወያኔ ቃል አቀባዮች መግለጫ ሰጥተዋል። የታጋዩ ሞት ከመሰማቱ በፊት ቃል አቀባዮቹ የግድያው ምክንያት "ተመራምረው" ደርሰውበት ነበር ማለት ነው። ፍርድ ቤት ተብየውም ቃል አቀባዮቹ የሰጡትን ብይን ነው የደገመው። የአቶ አረጋዊ መገደል ብቻ ሳይሆን ገዳያቸው ነው በተባለው ሰው ላይ የተወሰደውም የፍርድ አፈፃፀም የምርጫው አንዱ አካል ነው። ይህም የወያኔ ሁለተኛው ትምህርት መሆኑ ነው።

ወያኔ የትግራይን ሕዝብ ከተቀረው ኢትዮጵያዊ ለመነጠል ያደረገው ተንኮል ሲከሽፍበት ወደየት እንደሚያመራ መገመት አስቸጋሪ ቢሆንም ሁለት ነገሮች ካሁኑ ተለይተዋል እነሱም ግምባር በመምታት ፋንታ በእጅ አዙር ማስገደል እና በ97ም ውጤታማ የሆነበት የፍርድ ቤት ድራማውን አጠናክሮ መቀጠል ናቸው።

የመለስ ዜናዊ መቅበጥበጥ፤ በትግራይ የተንሰራፋው ሽብር፤ በእነ አቶ ስየ አብርሃ ላይ በትግራይ ከተሞችና ገጠሮች እየተነዛ ያለው አሉባልታ በጥምሩ ሲታይ ወያኔ ከምርጫ 97 በኋላ ያደረገውን መሰል አፈና ትግራይ ውስጥ ከምርጫው አስቀድሞ ሊያደርገው እየዳዳ ያለ ይመስላል።

የትግራይ ሕዝብና የትግራይ ተወላጅ ፓለቲከኞች ራሳቸውን ከወያኔ ከመለየትም አልፈው አማራጭ ሆነው መቅረባቸው መልካም ነገር ነው። ከዚህም በተጨማሪ ከሌላው የአገሪቱ ክፍል የዲሞክራሲ ኃይሎች ጋር ተባብረው መቆማቸው የሚያስደስትም፤ የሚያኮራም ተግባር ነው። የትግራይ ሕዝብም ወያኔ ለገዛ ራሱ ካልሆነ በስተቀር ለማንም ያልቆመ፤ በሥልጣኑ ከመጣበት ደግሞ ለማንም የማይመለስ ፀረ-ኢትዮጵያ ኃይል መሆኑን ዛሬ በግልፅ የሚገነዘብበት አጋጣሚ ተፈጥሯል። ፀረ-ኢትዮጵያ የሆነ ኃይል ፀረ-ትግራይም መሆኑ ዛሬ ያፈጠጠ ሃቅ ሆኗል።

ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ ቢደረግ ዘንድሮ ወያኔ የትግራይን ወንበሮች በሙሉ ሊያጣ እንደሚችል መለስ ዜናዊም የተገዘበው ይመስላል። በአንፃሩ ወያኔ ከትግራይ አንዲትም ወንበር ለማጣት የተዘጋጀ አይመስለንም። ስለዚህም በሰላማዊ ምርጫ በጉልበት የያዘውን የፌደራልም ሆነ የክልል ሥልጣን ይለቃል ብለን አናምንም። ያም ሆኖ ግን በምርጫ 97 የአዲስ አበባና ሌሎች አካባቢዎች ሕዝብ ለወያኔ ያስተላፈውን መልዕክት የትግራይ ሕዝብ በዘንድሮው ምርጫ ያስተላልፋል ብለን እንጠብቃለን። ከምርጫ በኋላ ደግሞ ወያኔ በጉልበት እንጂ በካርድ ሊባረር የማይችል አምባገነን መሆኑን ለትግራይም ሕዝብ ግልጽ ይሆንለታል ብለን እናምናለን።

በሌላ የኢትዮጵያ ክፍሎች ያለን ኢትዮጵያዊያን በምርጫ 97 ሞክረነው፤ ድምፃችንን የሚያከብርን አለመኖሩን ተገንዝበን ትግላችንን ወደ ሚቀጥለው እርከን አሸጋግረናል። ዘንድሮ ደግሞ የትግራይ ሕዝብ በተመሳሳይ ሁኔታ ግልጽ መልዕክቱን ያስተላልፋል፤ ቀጥሎም ትግላችንን ይቀላቀላል ብለን እናምናለን። የትግራይ ሕዝብ ከሌላው ወገኑ ጋር አብሮ መቆም ወያኔ ሊሸከመው የማይችለው ኪሳራ እንደሚያመጣበት እሙን ነው።

የምንናፍቃትና የምንወዳት ኢትዮጵያ ደግሞ ሕዝቦቿ ተፋቅረውና ተደጋግፈው የሚኖሩባት ነች። ይህችን ኢትዮጵያ እውን ለማድረግ በጋራ መነሳት ይኖርብናል።

አቶ አረጋዊ ገብረዮሃንስ፣ ወጣት ሽብሬ ደሳለኝ፣ ህፃን ነቢዩ አለማየሁ እና ሌሎች ስማቸውን ዘርዝረን የማንጨርሰው ኢትዮጵያዊያን የከፈሉት መስዋዕትነት መና አይቀርም።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ**

## ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ የሚፈጽመውን ሰቆቃ . . . ከገጽ 1 የዞረ

በዚሁ ስብሰባ ላይ የወያኔው አገዛዝ ወደስልጣን ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ እያደረሰ ያለው ኢሰብአዊ ተግባር እጅግ የሚዘገንን መሆኑ፡ ይህም በትውልድ ኢትዮጵያዊ በዜግነት ብሪታኒያዊ የሆነውን ህዝብ እጅግ እንደሚያሳስበው የተገለጸ ሲሆን የዩናይትድ ኪንግደም መንግስት አምባ ገነን ከሆኑት ዘረኞች ይልቅ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር እንዲቆምና መለስ ዜናዊና ግብረ አበሮቹ በህዝብና በሃገር ላይ ለሚያደርሱት ወንጀል ለፍርድ የሚቀርቡበት ሁኔታ እንዲፈጠር ተጠይቋል። ከዚህም ጋር በተያያዘ በዩናይትድ ኪንግደም የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ወደፊት መለስ ዜናዊ ወደ ለንደን ቢመጣ የዜግነት መብታቸውን በመጠቀም ርምጃ ለመውሰድ ዝግጁ መሆናቸውን አረጋግጠዋል።

የእለቱ የክብር እንግዳ ወ/ሮ አና ጎሜዝ በበኩላቸው ባደረጉት ንግግር በኢትዮጵያ የተካሄደው የ1997 ዓም የምርጫ ሂደት የማይረሳ መሆኑን በምሬት አስታውሰው የመለስ ዜናዊ አገዛዝም በሳቸውና በቡድናቸው ላይ በመንግስት መገናኛዎች ያካሄደውን የስም ማጥፋት ዘመቻ ማካሄዱን፤ በግልም ማስጠንቀቂያና ማስፈራሪያ ሳይቀር ይደርሳቸው እንደነበርና ለዚህ ማስፈራሪያም ምንም አይነት ቦታ ባለመስጠት ከኢትዮጵያ ህዝብ ጎን መቆምን እንደመረጡ ለተሰብሳቢዎች ገልጸዋል። በመቀጠልም በመለስ ዜናዊ የሚመራው የኢትዮጵያው አገዛዝ በሃሰትና በስርቆት የሚያምን አምባገነን በመሆኑ በ1977 በተከሰተው የርሃብ አደጋ ከዓለም አቀፉ ህብረተሰብ በነ ቦብ ጊልዶፍ ባንድ ኤይድ የተሰበሰበውን የርዳታ እህል በመሸጥ ገንዘቡን ለጦር መሳሪያ ግዢ ማዋሉ እንዳሳስገረማቸው የገለጹት አና ጎሜዝ ከዚሁ ድርጊት ባልተናነሰ ሁኔታ ዛሬም የወያኔው አገዛዝ የሃገሪቱን መሬትና ሀጻናት ሳይቀር በመሸጥ ላይ እንደሚገኝ በቁጪት ገልጸዋል። በመጨረሻም መጪው የ2002 ዓም ምርጫን በሚመለከት በኢትዮጵያ በምንም ዓይነት ሁኔታ የመለስ አገዛዝ ነጻና ፍትሃዊ ምርጫን ያካሂዳል ብለው እንደማያምኑ ገልጸው ኢትዮጵያዊያን በዘርና በፖለቲካ አመለካከት በመካከላቸው ያለውን ልዩነት በማስወገድ በጋራ ተነስተው የጋራ ችግራቸውን ማስወገድ እንደሚጠበቅባቸው አስገንዝበዋል።

ሌላው የክብር እንግዳ አባንግ ሜቶ ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ በኢትዮጵያ ከቶውንም ሊታሰብ የማይችል መሆኑን ገልጸው ባሁኑ ሰዓት ግልጽነትና ተጠያቂነት በሌሉበት ሁኔታ በሃገሪቱ የተለያዩ ክልሎች ዜጎች ላይ ኢሰባዊ በደልና ግፍ እየደረሰ ያለ መሆኑን እንዲሁም የአምባገነኑ መለስ አገዛዝ የምርጫ ስነምግባር ደንብ ማዘጋጀቱና ለምርጫው ትኩረት እንደሰጠ ለመምሰል የሚያደርገው ትግል ምእራባዊያንን ለማደናገር የሚጠቀመው ስልት ነው ብለውታል። በተመሳሳይ መልኩ የ3ኛው ዓለም ተብየው የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል የሆኑት ጋዜጠኛ ወ/ሮ ሳንድራ ሳተርሊ ባደረጉት ንግግር የኢትዮጵያው አገዛዝ በተለያዩ ወቅቶች የሃገሪቱ ኢኮኖሚ ያደገ መሆኑን ማቅረቡ ከእውነታው የተቃረነ ነው ካሉ በኋላ፣ በሃገሪቱ የሰብአዊ መብት አጠባበቅ ሁኔታም አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱን ጠቅሰው የመከባበር ባህልንና ጨዋነት ከተላበሰው የኢትዮጵያ ህዝብ ጎን ሁላቹንም መቆም ይገባናል ብለዋል፡፡

## ውጭ ጉዳይ ሲገለጥ

### ክፍል 2 ካለፈው የቀጠለ

ለመሆኑ ያ አንቶኖቭ ሙሉ ኤሌክትሮኒክስ በማን ገንዘብ ይሆን የተገዛው ? የመጓጓዣውንስ ወጭ ማን ከፈለ? እንግዲህ ይህንና ይህን የመሰሉትን የጎደፉ ተግባራት ስናይ ህወሃት ***ማፊያ*** ቡድን ነው መባሉ ትክክል ነው እንላለን።

በመጨረሻም ፈቃድ ሰጭው ከዚህ ክስተትና ከሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ከፈቃድ ሰጭነቱ ተነስቶ ተራ ሰራተኛ ሁኖ እንዲሰራ ከተደረገ በኋላ ከማያውቃቸው ሰዎች ስልክ እየተደወለለት ልዩ ልዩ ማስፈራሪያና የግድያ ዛቻ ይደርሰው ስለነበረ ልጆቹንና ባሌቤቱን ይዞ ተከብሮ የኖረበትን አገር ጥሎ ለመሰደድ ተገደደ።

***ሰራተኛ ቅጥር***

የመ/ቤቱ ክፍት የስራ ቦታዎች በማስታወቂያ ይወጣሉ አመልካቾች እንዲወዳደሩ ይደረጋል የቅጥርና የደረጃ እድገት ኮሚቴ ፈተና ያወጣል ይፈትናል የተሻለ ውጤት ያላቸው እንዲቀጠሩ ይወስናል። ከዚህ በኋላ በቅጥርና ደረጃ እድገት መመሪያ ውስጥ ያልተካተተ ሌላ ህግ ይመጣል። የኋላ ታሪክ ጥናት የሚባል። ይህን ጥናት የሚያጠናው አቶ ሃዱሽ ነው። ሃዱሽ የትግራይ ሰው ሲሆን የስራ መደቡ ጥበቃ ሰራተኛ ቢሆንም ዋናው ስራው ግን የአመልካቾችን የኋላ ታሪክ ማጥናት ነው። ሃዱሽ የአመልካቾችን የኋላ ታሪክ በየአድራሻቸው መሰረት በየቀበሌው ወይም በተማሩበት ኮሌጅ እየሄደ እዚያ ባሉት ወኪሎቹ አማካኝነት ልቅም አድርጎ አጥንቶ ሲያበቃ ይቀጠሩ ወይም አይቀጠሩ የሚለውን የመጨረሻውን ውሳኔ ይሰጣል።

አንድ ቀን አቶ ሃዱሽ የቢሮየን በር ክፍቶ ገባና ሞባይል ስልኮች ላይ እና ከአዲስ አበባ ውጭ ስልክ መደወል እፈልጋለሁና ቀጥታ ስልክህን ልጠቀም አለኝ። ፈቀድኩለት። ስልኩን ማይክራፎን ላይ አድርጌ ወደ ፊቱ ቀረብ አደረኩለት።እርሱም የስም ዝርዝር የተጻፈባቸውን ወረቀቶች አውጥቶ ስልኮቹን መደዋወል ጀመረ። የሚያወራው በትግሪኛ ነው። ይህን የእነርሱን የሚስጥር ቋንቋ ባለመቻሌ ባዝንም ደርግ ኢሰፓ፤ አብዮያዊ ዴሞክራሲ አመለካከት፡ህገ-መንግስት፡ ፖለቲካ ምና ምን ይል ስለነበረ ምን ለማወቅ እንደሚፈልግ ለመገመት አልቸገረኝም።

ይህ በእንዲህ እንዳለ አንዱን በአማርኛ ማውራት ጀመረ። አሁን በንቃት ማዳመጥ ጀመርኩ። ንግግሩን እንዳለ አቀርበዋለሁ፡

"ሃሎ! ማነህ አንተ!? ስሙን የማላስታውሰውን ሰው ስም ጠርቶ እገሌ ነህ ?"
"አይደለሁም"
"እግሌ አለ ?"
"አዎን"
"እስኪ አቅርብልኝ"
"ሃሎ ማን ልበል" አለ አንድ ትህትና ያለው የሚመስል ሰው ከወዲያ ማዶ
"ሃዱሽ ነኝ ያንን ነገር ጨረስክ"
"አዎን አዎን"
"ደህና በል ንገረኝ እስኪ አመለካከቱ እንዴት ነው ?"
"ጥሩ ነው"
"ዋ! ከኦነግ ጋር የሚመሳሰል አቋም አለው ብለውኛል እኮ"
"እኔ እርሱን አላውቅም"
"እንዴት አታውቅም ?"
"እኔ የማውቀው አዲስ አበባ ተውልዶ ማደጉንና 6 ኪሎ ዩኒቨርሲቲ መመረቁን ነው"
"ኦሮሞ አይደልም እንዴ ?"
"ነው"

"ታደያ ከኦነግ ጋር ግኑኝነት የለውም ትላለህ?" ***(ይህን ስሰማ የኦነግን ነገር ማሰላሰል ያዝኩ፤ ምነወ ኦነግ ለኦሮሞ ህዝብ ችግር መድረስ አቃታዉ ? በኦነግ ስም በኢትዮጵያዊያኑ ላይ ልዩ ልዩ በደል ሲፈፀም ይህን ግፍ ለማስቆም ምነዉ አቅም አጣ? እ ያልኩ ራሴን መጠየቅ ጀመርኩ፤ ኦነግ የኦሮሞን ችግር የማይፈታዉ እኔንና ሌሎች ጭቁን ድሃ ህዝቦችን ስላገለለ እኛም በፍርሃት ስለምናየው ነዉ ብየ ለራሴ ነገርኩት። ከዚህ ውጭስ ሌላ ምን ምክንያት ይኖረዉ የሆን ?)*** ።ንግግሩ ይቀጥላል፤

"እኔ የማውቀው የአዲስ አበባ ልጅ መሆኑን ነው እንጂ አንተ ሰለምትለው ነገር መረጃ የለኝም"
"እሺ ውጭ አገር ዘመዶች አሉት ?"
"አዎን አሉት አሉ"
"የእነርሱስ አመለካከት"
"ማለት ?"
"እነርሱ ተቃዋሚን ይረዳሉ የሰማሓው ነገር የለም ?"
"የሰማሁት ነገር የለም"
"ኢህአዴግ በሚጠራው ስብሰባ ላይ ይመጣል ?"
"መጥቶ አያውቅም"
"ታዲያ የአመለካከት ችግር አለበት ማለት ነዋ !"
"እኔ እንጃ"
"ምን እኔ እንጃ ትላለህ ይሄን ይሄን ነው እኮ ማጥናት የነበረብህ"
"እኔ የማውቀውን ነግሬሃለሁ"
በል ድህና ሁን ብሎ መልስ ሳይጠብቅ ስልኩን በጆሮዉ ላይ ዘጋው።

ሶስት ሳምንት ፈጅቶ የረባ መረጃ አላመጣም ብሎ ሲናደድ እኔ ተቀብየ ያናገርከው ሰው የአመለካከት ችግር ይኖርበት ይሆን ? ስለዉ ***"ይሄ በዚኔ ምን አመለካከት አለው እሱ ደግሞ*** እዚያ ቀበሌ ውስጥ ስራ ቢሰጠውም በአግባቡ መወጣት አልቻለም። ዝም ብሎ ነው አይረባም" ብሎ ሲያበቃ ሌላ ስልክ መደወል ጀመረ። አሁን የሚያወራው በትግሪኛ ነው እኔ በማልሰማው የእርሱ የሚስጥር ቋንቋ። ከዚህኛው ሰው ጋር ሲያወራ የሚፈልገውን የሚያገኝ ይመስል ነበር። ሁሉንም የአገሪቷን ቁልፍ የስልጣን ቦታዎች ጨካኝ የተወሰኑ ትግሬዎች ይዘዉ የአገሪቷን ስቃይ ማብዛታቸዉ ሳያንስ እንዲህ በየቦታዉ ተሰግስገው የቀሪውን ኢትዮጵያዊ እድል ፈንታ ወሳኝ ሁነው መቀመጣቸው ውስጤን ሲበላው ተሰማኝና ከሃዱሽ በስተረጅባ ያለውን ያን ዘረኛ ስርአት አጥብቄ ጠላሁት።

ሃዱሽ ስልኩን ደውሎ እንደጨረሰ ስም በተጻፈበት ነጭ ወረቀት ላይ አጫጭር ነጥቦችን ጽፎ ሲያበቃ የተወዳዳሪዎቹ ስም በተጻፈበት ስንጠረዥ ላይ ደግሞ በስማቸው ትይዩ የ"ኤክስ" እና "ራይት" ምልክት ያደርግባቸዋል። ይህን የሚያደርገው ፊቴ ቁጭ ብሎ ስለሆነ የ"ኤክስ" ምልክት ሲያደርግ ያየሁትን የአንዱን አመልካች ሁኔታ ጠየኩት፡፡

እሱ የ"x" ምልክት ያደርክበት አይሆንም ማለት ነው?
"አዎን አይሆንም"
ምነው ?
"ችግር አለበት"
ምንድ ነው ችግሩ ?
"ምን ይሄ ትምክህተኛ ነው። ዩንቨርሰቲ እያለ ደግሞ ይበጥብጥ ነበር። ጸረ ህዝብ ነው።የአመለካከት ችግር አለው።አባቱ ደግሞ ደርግ ኢሰፓ ነበር"
ስለዚህ አይቀጠርም ማለት ነው ?
ምን አንተ ደግሞ የዚህን መ/ቤት ጸባይ እያወክ ትጠይቀኛለህ? ሲለኝ እርሱ የሚያውቀውን የመ/ቤቱን ጸባይ ባለማወቁ እያዘንኩ ሌላ የ"ራይት" ምልክት ያደረገበትን ጠየኩት፤
እርሱ የ"ራይት" ምልክት ያደርክበት ጥሩ ነው ?
"ይሄ ደህና ነው። የአርሶ አደር ልጅ ነው። ዩነቨርስቲም እያለ ከት/ቱ በቀር ሌላ ምንም አያውቅም። ዝምተኛ ነው"
ለመሆኑ ህገ መንግስቱን በሙሉ ልቡ ይደግፋል ?ስል ጠየኩት፤
"ወዶ ነው የት አባቱ ይሄዳል ብለህ ነው ?"
አይ እንደው ዝምተኛን ሰው ማመን ይከብዳል ብየ ነው።
"እዚህ ከተቀጠረም በኋላ አመለካከቱን እንከታተላለን ምን ችግር አለ ብለህ ነው ?"

አዎን እንደሱም ይቻላል ለካ። (ከቅጥር በኋላ በሚደረግ ክትትል በርካታ ሰራተኞች እንዲባረሩ ተደርጓል)

የብዙ ብሄሮች አገር በሆነች ኢትዮጵያ ውስጥ ውጭ ጉዳይን በመሰለ መ/ቤት ተመጣጣኝ የብሄር ተዋፅኦ መኖር ሲገባዉ ዋናዉ መ/ቤትና ኢምባሲዎች በትግራይ ብሄር አባላት በብዛት ተይዘዋል። አገሪቷ ባላት ከ35 በላይ በሚሆኑ ኢምባሲዎች ውስጥ ትግሬ የሌለበት ኢምባሲ አይገኝም። በያንዳንዱ ኢምባሲ አንድ ወይም ሁለት ትግሬ ተሹሞ እንደፈለገ ይሆናል። ዘበኛ እንኳ ቢሆን ሌሎች ዲፕሎማቶችን የማዘዝ መብት ያለው ታጋይ ብዙ ነዉ።

በዋናዉ መ/ቤት ደግሞ ሊኖር ከሚገባዉ በላይ የትግራይ ካድሬዎች ተሰግስገዉበታል። አብዛኞቹ በትግል ሜዳ የነበሩና ይህ ነዉ የሚባል ችሎታ የሌላቸዉ ፍፁም ደካማዎች ሲሆኑ ግሩም የሆነ ችሎታ ያላቸዉ ጥቂት የትግራይ ሎጆች እንዳሉም ምስክርኔቴን እሰጣለሁ።

መስሪያ ቤቱ ባሉት የዋና ዳይሬክተር ቦታዎች ዋና ዋና ቁልፍ የሃላፊነት ቦታዎች በትግራይ ብሄር አባላት ተይዘዋል። ዋና ዋናዎችን ለማሳት ያህል ሙሉጌታ ዘዉዴ የሚንስትሩ ካብኔ ዋና ዳይሬክተር፤ ፍስሃ ተስፉ ዋና አማካሪ፤ ዋህደ በላይ የመስሪያ ቤቱ የህዝብ ግኑኝነት ዋና ዳይሬክተር፤ መብራት በየነ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ጉዳዮች ዋና ዳይሬክተር በመሆን ቦታ ቦታቸውን ይዘዋል።

የመ/ቤቱ (የመጋቢት 30 1996 ዓ.ም) የሰዉ ሃይል ስርጭት ስታትስቲክስ የሚከተለዉን ይመስል ነበር።

| | |
|---|---|
| ኦሮሞ | 54 |
| አማራ | 69 |
| ትግሬ | 52 |
| ጉራጌ | 42 |
| ሌሎች | 52 |

የህዝብ ቆጠራ መረጃ እንደሚያመለክተዉ የትግራይ ህዝብ ከሲዳማ ከወላያታ ወይም ደግሞ ከጉራጌ ተመጣጣኝ ቢሆንም ከሰንጠረዡ እንደምናየዉ የትግሬዎች ቁጥር ከኦሮሞ በልጦ እናገኛለን። በዚህም በዉጭ ጉዳይ መ/ቤት "proportional ratio" አዉጥተን ስናይ የትግራይ ብሄር አባላት የአንደኝነትን ቦታ ይዘዋል። ይህ የሆነዉ ደግሞ ልዩ ችሎታ ስላላቸዉ ሳይሆን የሌሎች ብሄር አባላት በቅጥርና ደረጃ እድገት ኮሚቴ የሚሰጠዉን ፈተና በከፍተኛ ውጤት ቢያልፉም ልዩ ልዩ ስም እየተለጠፈባቸዉ እንዳይቀጠሩ በመደረጉና የተቀጠሩትም በተለያየ ምክንያት ከመ/ቤቱ ስለሚባረሩ ነው።ይህ መ/ቤት ከመከላከያ ሚ/ር ቀጥሎ የመንግስት ከፍተኛ በጀት የሚመደብለት መ/ቤት ሲሆን የዚህ በጀት ተጠቃሚዎች ደግሞ እነዚሁ ካድሬዎች ናቸዉ ማለት ነዉ።

ክፍል 3 በሚቀጥለው ሳምንት ይቀርባል

## የቴሌኮሚኒኬሽን ሰራተኞች በመጭው ምርጫ የሚጠበቅባቸውን ድርሻ ለመወጣት ዝግጁነታቸውን መግለጻቸውን የአገዛዙ የመገናኛ ብዙሀን ገልጸዋል

ሪፖርተራችን ከአዲስ አበባ በላከው ዜና እንደገለጸው የቴሌኮሚኒኬሽን ሰራተኞች ዝግጁነታቸውን አጠናቀው የምርጫውን መጀመር እየተጠባበቁ እንደሚገኙ ይፋ አድርገዋል ። የቴሌ ሰራተኞቹ ዜና እንደተሰማ በኢትዮጵያ በሞባይል መልእክት መላላክ ሊታገድ ነው የሚል ወሬ በስፋት በከተማው እየተሰራጨ ነው። ሪፖርተራችን በላከው ዜና የቴሌ ሰራተኞቹ ዝግጁነት አላማ በአንድ በኩል በሞባይል መረጃ የሚለዋወጡትን ለማደን፣ በሌላም በኩል ጽሁፍ በኢንተርኔት የሚጽፉትን አድኖ ለመያዝና የሬዲዮ ስርጭቶችን ለማፈን ነው ሲል ገልጿል።

የወያኔ አገዛዝ ከግንቦት 97 ምርጫ በሁዋላ መልእክቶች በሞባይል እንዳይተላለፉ አግዶ እንደነበር የሚታወስ ሲሆን፣ የቴሌኮሚኒኬሽን ሰራተኞች ዝግጁነት ዜናም ይህንን ህገ ወጥ ድርጊት ለመድገም ታስቦ የተነገረ መሆኑ በስፋት ይታመናል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ የአሜሪካ፣ የጀርመንና የግንቦት7 ድምጾች አፈና እንደተደረገባቸው ሲፒጄን የመሳሰሉ አለማቀፍ ተቋማት መግለጻቸው ይታወሳል።

## የኢትዮጵያ ቴሌቪዥንና ራዲዮ ጋዜጠኞች በምርጫ ውጤት ሪፖርት አደራረግ ላይ ስልጠና እየወሰዱ ነው ተብሎአል

ስልጠናውን የሚሰጡት ዶ/ር ገብረመድህን ስምኦን የተባሉ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህር ሲሆኑ ፣ እኚሁ ግለሰብ በ1997 ምርጫ ህወሀትን ወክለው በቦሌ ክፍለ ከተማ መወዳደራቸውና መሸነፋቸው ይታወቃል። ጋዜጠኞቹ ከምርጫ 97 ልምድ በመማር በገጠሪቱ የኢትዮጵያ ክፍሎች ተሰማርተው ስለምርጫው ውጤት ዘገባ እንደሚያቀርቡ ይጠበቅ እንጅ ዋናው ተልእኮዋቸው በአገሪቱ ተሰማርተው የአገዛዙ ዳገፊዎችን ደጋፊዎች ካልሆኑት መለየት ነው ተብሎአል።

ከምርጫ 97 በሁዋላ በርካታ አገዛዙን ሲያገለግሉ የነበሩ የስፖርት ጋዜጠኞች እንኳን ሳይቀሩ አገር ጥለው መጥፋታቸው ይታወሳል።

## ኢትዮጵያ ወደ ወታደራዊ አገዛዝ እየገባች ነው . . . ከገጽ 1 የዞረ

ህዝቦች በአንድነት ከተሰባሰቡ ለአምባገነኑ አገዛዝ ፍርሀት ይፈጥራሉ ምክንያቱም፣ በአንድነት ከተገናኙ ስለመንግስታቸው ያወራሉ፣ በዚህም የተነሳ አገዛዙ ባለፈው አመት በአፍሪካ ውስጥ እጅግ ጨቋኝ የሚባለውን መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን የሚመለከተውን ህግ አውጥቷል ብሎአል። በሰብአዊ መብቶች ዙሪያ የሚሰሩ ድርጅቶች እንዲዘጉ በመደረጋቸው፣ በአገሪቱ ውስጥ በሴቶች ላይ አስገድዶ መድፈር ሲፈጸም፣ አለፍላጎታቸው ጋብቻ እንዲፈጽሙ ሲደረግና የተለያዩ ወንጀሎች ሲፈጸሙባቸው ጥብቅና የሚቆምላቸው ድርጅቶች የለም ሲል ኢንዲፐንደንት በዘገባው መለስ ዜናዊ ዲሞክራሲን አስፍኛለሁ እያሌ ለጋሽ አገሮችን የሚያታልልበትን የሃሰት ፕሮፖጋንዳ በማጋለጥ አገዛዙን ክፉኛ ኮንኖአል።

## አምባገነኑ መለስ ዜናዊ ፎቶ ግራፉን በየከተሞች . . . ከገጽ 1 የዞረ

ጉዳዮች በማዋከብ ላይ እንደሚገኝ ሪፖርተራችን ገልጿል። ወጣቶች ለስራ መፍጠሪያ በሚል ሰበብ ገንዘብ በገፍ እንዲወስዱ እየተደረጉ ሲሆን፣ ይህም አልበቃ ብሎ በወጣቶች ሊግ፣ በወጣቶች ፎረም፣ በዩኒቨርሰቲና ምመህራንና ተማሪዎች አማካኝነት ስብሰባዎችና ስልጠናዎች እየተሰጡዋቸው ነው ሲል የአዲስ አበባው ሪፖርተራችን ገልጿል።

## በባህርዳር እና በመቀሌ ከተሞች ወታደራዊ ሹም . . . ከገጽ 1 የዞረ

የሰሜኑ ህዝብ ከወያኔው አገዛዝ ጋር ሆድና ጀርባ እየሆነ መምጣቱን ተከትሎ በአካባቢው በርካታ ሰራዊት እየሰፈረ እንደሚገኝ ወታደራዊ ምንጮቻችን አክለው ገልጸዋል።

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በአማራ ተወላጅ ወታደራዊ መኮንኖች ላይ ያለው እምነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሸረሸረና ጥርጣሬውም ከፍ እያለ በመምጣጡ፣ አካባቢው በትግራይ ወታደራዊ መኮንኖች እዝ ስር እንዲሆን እንቅስቃሴ መጀመሩን ምንጮቻችን አክለው ገልጸዋል።

ከሳምንት በፊት በባህርዳር ከተማ በተደረገው ስብሰባ አስገራሚው ነገር የጥበቃው ሁኔታ ነበር ያሉት ምንጮቻችን፣ ከ10 በላይ መትረዬስ የጫኑ ላንድ ክሩዘሮች፣ የፌደራልና የክልል ፖሊሶች እንዲሁም በርካታ የመከላከያ ሰራዊት አባላት ተሳተፈውበታል ብለዋል። ስብሰባው እየተደረገ በነበረበት ወቅት በአካባቢው ሰዎች እንዳያልፉ፣ በድንገት በአካካቢው የታዩ ሰዎች ከፍተኛ እንግልት ይደርስባቸው እንደነበር ያገኘነው መረጃ አመልክቷል።

በተያያዘ ዜናም ለፌደራልና የክልል ፖሊሶች ከሻለቃነት እስከ ኮሎሌልነት የሚደርሱ ማእረጎች እንደተሰጡዋቸው ሪፖርተራችን ከአዲስ አበባ ዘግቧል። ማእረጉ የተሰጣቸው የአገዛዙ ታማኝ ፖሊሶች ሲሆኑ፣ በሆነ አጋጣሚ ከምርጫው ጋር በተያያዘ ረብሻ ቢነሳ እርምጃ ለመውሰድ የሰለጠኑና ዝግጁነታቸውን የገለጹ መሆናቸው ታውቋል።

## የወያኔ የደህንነት ባልስልጣን ጌታቸው አሰፋ . . . ከገጽ 1 የዞረ

እንደ ውስጥ ምንጮቻችን መረጃ የዘረኛው መለስ ቀኝ እጅ እንደሆነ የሚነገርለት ጌታቸው አሰፋ ትእዛዙን ለመስጠት የተገደደው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በህዝቡ ዘንድ እየታየ የመጣው ስሜት አገዛዙን ከፍተኛ ወደ ሆነ የፍርሀት ውቂያኖስ ውስጥ እየከተተው በመምጣቱ ነው ተብሎአል። የአፈናው እርምጃ በሁለት መንገድ እንደሚጀመር የተናገሩት ምንጫች፣ በአገር ውስጥ በተለይም መድረክ በተባለው የተቃዋሚዎች ስብስብ አባላትና ደጋፊዎች በሆኑት ላይ ማስፈራራትና ስውር የሆነ እርምጃ እንዲወስዱ ፣ በውጭ አገር ሆነው የምርጫውን ሂደት ለማበላሸት በሚሯሯጡት ሀይሎች ላይ ደግሞ በተከታታይነት ሪፖርት እንዲያቀርቡና በሚኖሩባቸው አገሮች አማካይነት ዲፕሎማሲያዊ ጫና እንዲፈጠር ማድረግ እንዲቻል፤ ከተቻለም በየኮሚኒቲዎች ውስጥ ሰርጎ በመግባት ደጋፊዎቻቸውን መከፋፈል እንደሚያስፈልግ መገለጹ ታውቆአል።

የወያኔ አገዛዝ በግንቦት97 ምርጫ ወቅት ሲያደርገው እንደነበረው የአፈናውን ስራ ምርጫው ከተካሄድ በሁዋላ ከማድረግ ይልቅ ካሁኑ አንዳንድ እርምጃዎችን በመወስድ ለማፈን እቅድ እንዳለው የተናገሩት ምንጮቻችን፣ በተለይም በመድረክ አባላት ላይ የተለያዩ የክስ አይነቶችን ማከማቸት መጀመሩን ለማወቅ ተችሎአል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ መለስ ዜናዊ በድህረ ምርጫ 97 የአዲስ አበባን ንጹሃን ዜጎች እንዲጨፈጭፉ ልዩ ስልጠና አሰጥቶ ያሰማራው የአጋዚ ሃይል በሀረሪ፣ ድሬዳዋና ጂጂጋ አካባቢዎች ሰዎችን መግደል መጀመሩን ለማወቅ ተችሎአል። ከሁለት ሳምንት በፊት ካፒቴን እሸቱ መንግስቴ የተባሉና በወያኔ አገዛዝ ላይ ከፍተኛ ተቃውሞ በማሰማታቸው ይታወቁ ሰው፣ በደህንነት ሃይሎች ታፍነው ከተወሰዱና አሰቃቂ ድበደባ ከተፈጸመባቸው ቦኋላ አስከሬናቸው በሜዳ ላይ ተጥሎ መገኘቱን ከስፍራው የተገኘ ዜና አጋልጦአል። በተመሳሳይም አቤል ኩባ እና ደረጀ ሙሉጌታ የተባሉ የወያኔ ተቃዋሚ ወጣቶች በፖሊስ ተወስደው እስከዛሬ የደረሱበት ቦታ አለመታወቁን ኒውስ ድሬ የተባለ ድህረ ገጽ ገልጿል። በርካታ የአካባቢው ነዋሪዎች ወጣቶቹ በነፍስ በላው የመለስ ዜናዊ ገዳይ ኮማንዶ ተገድለው አስከሬናቸው ሆን ተብሎ እንዳይገኝ እንደተደረገ ያላቸውን ጥርጣሬ እየገለጹ መሆናቸውን ለማወቅተ ተችሎአል። ከ3 ሳምንት በፊት በትግራይ ክልል የአረና አባልና የፓርላማ ዕጭ ተወዳዳሪ በነበሩ በአቶ አረጋዊ ገብረ ዮሀንስ ላይ ተመሳሳይ የወንጀል ድርጊት በገዛ መኖሪያ ቤታቸው ውስጥ እንደተፈጸመ፤ ህዝቡ የወንጀል ድርጊቱን አምርሮ በመቃወሙ የተነሳ ህዝባዊ ተቃውሞውን ለማብረድ ሲባል ገዳይ የተባለው ግለሰብ በአገሪቱ የወንጀል ፍርድ ቤቶች ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ፍጥነት የ15 ዓመት እስራት እንዲፈረድበት እንደተደረገ የሚታወስ ነው።

በተያያዘ ዜናም የአዲስ አበባው ሪፖርተራችን ወያኔ በእየቤቱ በመስጠት ላይ ያለውን የምርጫ መቀስቀሻ ጽሁፍ አጣቅሶ እንደላከው ፣ አገዛዙ አሁንም የተቃዋሚ አባሎችን የቀለም አብዮት ለማድረግ የተዘጋጁ ናቸው ናቸው ሲል እንደሚከስ አመልክቷል።

የቦሌ ክፍለከተማ የወያኔ / ኢህአዴግ ጽህፈት ቤት ለምርጫ ቅስቀሳ በየሰው ቤት በበተነው ወረቀት ተራ ቁጥር 10 ላይ “ **ምርጫውን በሁከትና አመጽ ታአማኒነቱን ለማጥፋት የሚንቀሳቀሱትን የቀለም አብዮተኞችን የሚታገልና የህዝብ ድምጽ የሚያከብር ፓርቲ ኢህአዴግን ይምረጡ**” የሚል አንቀጽ ሰፍሮ እንደሚገኝ አመልክቷል።

እንዲህ አይነት የቅስቀሳ ጽሁፎች በግንቦት97 ምርጫ ወቅት እንደታየው ተቃዋሚዎችን "**እንተርሃምዌ ዎች ናቸው**" በሚል ውንጀላ ለመምታት እንዳመቻቸው ሁሉ አሁን ደግሞ "**የቀለም አብዮተኞች**" በሚል ቅጽል ከወዲሁ ለሌላ ዙር ጥቃት እርምጃ እራሱን እያዘጋጀ መሆኑን ያመለክታል ሲል ሪፖርተራችን ከአዲስ አበባ ገልጿል።

## የአሜሪካን ስቴት ዲፓርትሜንት በኢትዮጵያ . . . ከገጽ 1 የዞረ

የስቴት ዲፕርትመንት አመታዊ ሪፖርት ወ/ት ብርቱካንን ጨምሮ በርካታ የፖለቲካ እስረኞች በእስር ላይ እንደሚገኙ የገለጸ ሲሆን፣ በእስር ቤት ውስጥ በወ/ት ብርቱካንና በሌሎችም እስረኞች ላይ ከፍተኛ የሆነ ግፍ መፈጸሙን ጠቁሟል።

በዚህ በስፋትና በዝርዝር በቀረበ ዘገባ የወያኔው አገዛዝ በአገሪቱ ውስጥ ያለውን የተበላሸ የሰብአዊ መብቶች አያያዝ ለማስተካከል ምንም አይነት በቂና አበረታች እርምጃ እየወሰደ አለመሆኑም ገልጿል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**በ 7530 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ** እና **በ 9610 KHZ በ 31 ሜትር ባንድ** ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።



**ውድ አንባቢያቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን g7radio@ginbot7.org ወይም በስልክ ቁጥር 0044- 203-286- 9661